እንኳንስ ሲሸጡን ሲዋዋሉብን እናዎቃለን።

የመልስ መልስ ለአቶ አብርሃ ደስታ

ከጎሹ ገብሩ

ለተከበሩ አቶ አብረሃ ደስታ በመጀመርያ የከበረ ሰላምታየን አቀርባለሁ በአካል ባንተዋወቅም በተጋድሎ ሃርነት ትግራይ ተብየዋ ትዕዛዝ ዘብጥያ በወረዱበት ወቅት የሚያውቅዎትም ሆነ የማያውቅዎት አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሙሉ በተሰነዘረብዎት ጥቃት ዘርና አካባቢ ባልለየ መልኩ ከጎኖ እንደተሰለፈ ይዘነጉታል ብየ አልገምትም እኔም እንደሌላው ሁሉ ነፃ የሚወጡበት ቀን ስመኝልዎት የነበርኩ ስሆን ህልሙ እውን ሆኖ ይህን ልብ የሚሰብር አጭር ትረካ ለመፃፍ እንኳን አበቃዎት እላለሁ።

በፃፉት ፅሁፍ ላይ እንደገለፁት እኔ የታሰርኩበት ምክንያት ወደ ብሔርና ጎሳ የወረደ አቋም ባለመያዜ ነው ብለዋል እንዲህ ዓይነቱ አቋም ባልከፉ ነበር ነገር ግን በተለያዩ ግዚያቶች የፃፏቸው መጣጥፎች ሲመረመሩ ግን አብዛኛዎቹ ትረካዎች በትግራይ አካባቢ ተፈጸሙ የሚባሉትን ትናንሽ ችግሮችን እንደ የአስተዳደር ችግሮች፤የውሃ እጦት፤የመሰብሰብያ አዳራሽ እጦትና እርስዎ በሚመሩት ድርጅት ዙርያ የተሰባሰቡት አባሎችዎ በሽፍታዋ ድርጅት የሚደርስባቸው በደልና መንገላታት በቅድሚያ በቁጭት ይተቻሉ። ይህ ማለት የብሔርና የጎሳ ጭምብልተኝነት የማያሳይ ከሆነ የሌላው አካባቢ ህብረተሰብ ት.ሓ.ሕ.ት የምትፈፅመውን በደል፤ዝርፍያ፤አንዱን ዘር በማጥፋት ሌላውን መተካት፤ሌላው ጥሮና ግሮ ያቆመውን ንብረት ለራሷ ጎሳ በመስጠት ጎዳና አዳሪ ያደረገችው ህብረተሰብ ተበደልኩ በሎ በመጮሁ መንደርተኛ የሚያሰኙት መስፈርቶች ከምኑ ላይ ነው ይላሉ? የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ እያሰማው ያለው ጭሆት ስለብሔሩ፤ ስለ ጎሳውና ህብረ ብሔሩ ሳይሆን ማንነቱ፤ ስብዕናዬና የመኖር ተስፋየ ጨለመብኝ የትግራይ ዜጋ የሆነ በተወለደበትና እትብቱ በተቀበረበት የመኖር መብቱ ሲከበርለት እኛ ግን በደደቢት ሽፍቶች ጥፋት ተፈርዶብናል እና ጨርሰው ሳያጠፉን ተሎ ድረሱልን አልን እንጅ እንደ ዘመናዮቹ ሁሉ መንገድ ይሰራልን፤አውሮፕላን መረፍያ ይጠረግልን ወይም ዘመናዊ ፋብሪካና የንፁህ ውሃ አቅርቦት ይደረግልን መች አልን። ድረሻችን ከሆነው መሬት በሰላም እንኑርበት እናንተም ድርሻችሁን ይዛችሁ እንደ ጥንቱ ጀርባዎችንን እየተካከክን በሰላም በጉርብትና እንኑር። የማንነት ጥያቄ መጠየቅ ዘረኝነት ሊያሰኝ አይገባም። አቶ አብርሃ ዘረኝነት ተጠፍጥፎ የተሰራው ተግራይ ውስጥ መሆኑ እያወቁ በሌላው ሕዝብ ላይ ማላከኮ ከአንድ ሙህር ግለሰብ ሊጠበቅ የማይገባ የተሳሳተ ምስክርነት መስጠት ተቀባይነት አይኖረውም።

መሬት የሉዓላዊነት መጠርያ ነው የሚል ሃሳብ ሰንዝረዋል በርግጥ ሉዓላዊንት በሥነ ስርዓቱ ቢተረጎም የጋራችን ለምንላት ኢትዮጵያ የተለያዩ የአስተዳደር ሥርዓቶች ቢለዋወጡባትም በመካከሉ የአስተዳደር ብልሹነት፤ፍርድን ማጓደል፤በሙስና መባለግ፤ማሰርና መግደል ቢከሰቱም ቅሉ አንድ ነገር መዘንጋት የማይገባን ሃቅ ግን ያለፉት መንግስታት የኢትዮጵያ ዳር ደንበሯን፤ክብሯንና ማንነቷን አሳልፈው ለጠላት ያልሸጡ ለመሆናቸው ታሪክ ሳያስተምርዎት የቀረ አይመስለኝም። አሁን ሥልጣን ላይ የተጣበቀው መዥገር ቡድንተኛና አገር አምክን የሽፍቶች ስብስብ መንግስት ሊያሰኙት የሚችሉ ባህርያት የለለው መንግስት ብለው የክብር ሥም መስጠትዎ በጣም ያስተዛዝባል። እንደ አንድ የፍትህ ተሟጋችነትዎ ሕዝብ ከአያት ቅድመ አያት እየተሸጋገረ ሲጠቀምበት የኖረውን ድርሻውን የሆነውን ለም መሬት ምክንያት እየተፈለገ ሲነጠቅና ለተወሰኑ የወርቅ ዘሮች ለመጥቀም ተብሎ የተሰራው የመሬት ስሪት ትግሬዎች ቢወስዱት የት ይሔዳል የሚል ሃሳብ መሰንዘርዎ ለማን ለመጥቀም እንዳሰቡ ህልም ፈች አያስፈልግም። ያ

ጭዋ የወልቃይት ጠገዴና የጠለምት ህዝብ የመሬቱ ባለ ቤት በነበረበት ወቅት ለብቻየ ልጠቀም ሳይል ከሌላው አካባቢ ለሚመጡ የህብረተሰብ አካል በችግር ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሁሉ አቅፎ፤ ደግፎ፤ደጉሞና መጠለያ ሆኖ እንግዳ የሚያስተናግድ ብቻየ ልብላ የማይለውን ሕዝብ ጥሮ ግሮ ያቆመው ርስቱ ተቀምቶ በተወለደበት አካባቢ እንዳይንቀሳቀስ አጥር ተሸክሎበት የትም መፈናፈኛ በማጣቱ የመኖር ተስፋው ጨልሞበት የደደቢት አውሬዎች የሚፈፅሙበት ግፍና በደል አልበቃ በሎ በየ ዱር ገደሉ፤ በባህረ ሰላጤው የአሳና የአሞራና ቀለብ ሁኗል። የዚህ ሁሉ በደል መነሻ እያወቁ ማንነቱ ይከበርልኝ ብሎ አቤቱታ ያቀረበውን ህብረተሰብ የወረደ ብሄርና ጎሳ አምላኪ ብለው ከመውቀስ ይልቅ እንደ ኢትዮጵያዊነት ማዕረገዎ ዋልታና ማገር ሆነው በደሉን ከትክሻው ለማላቀቅ መፍትሄ መሻት ይገባዎት ነበር እንጅ ለ26 ዓመት ሙሉ ያሰለቸውን የተ.ሃ.ሕ.ት ሙዚቃ ደግመው ደጋግመው ማስተጋባቱ ከአንድ ለህዝብ ሙብት የሚከራከር ግለሰብ የሚጠበቅ ተግባር አይደለም። አሁን በግልፅ ያለ ምንም ይሉንታ ይህች ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራት አገር በተወሰኑ ትግራይ በቀል የቤተሰብ ትሥስር በተቆራኙ የጥፋት መልዕክተኞች መዳፍ ሥር ላይ በመውደቋ ከአያት ቅድመ አያት ለዘመናት በመከባበር የኖሩትን ሕብረተሰዎች እርስ በራሳቸው በማጋጨት፣አንዱ ሌላውን እንዲወርና ከቀየው እንዲፈናቀል ከርቢት በመጫር ወላፈኑ እንዲፋፋም በማድረግ የህዝብ ሥቃይ ማየቱ የሚያዝናናትና የሚያረካት ዕኩይ የሆነች ድርጅት ካለፉት መንግስታት ሥር ተርታ ማስቀመጡ ትዝብት ላይ የሚጥል ነው። የትግራይ ህዝብ የተጠቀመው ነገር የለም ለሚው አስተያየትዎ በእርግጥ ሁሉም ዘራፊ ሊሆን አይችልም ነገር ግን እንበል ስወስት ሚልየን የተ.ሃ.ሕ.ት ደጋፊ አባሎች ቢኖሩ በአንድ ጨረቃ ምሽት የከበሩ ቢሊየነር ባለ ሀብቶች የቀረውን ሕዝብ መመገብ ስለሚችሉ የትግራይ ሕዝብ በመጠኑ ሳይጠቀም የቀረ አይመስለኝም። ሌላው ጥቅምም በመሳርያ ሃይል የተቀማው የወልቃይት፤ ጠገዴና ጠለምት ለም መሬት ላይ ሕዝብን ከቦታው በማፈናቀል አንድ ሚልየን የሚገመት የትግራይ ሕዝብ በማስፈር በስሎና ተጋግሮ የቆየውን የህዝብ ንብረት በመቀማት ተጠቃሚዉ ማን እንደሚሆን ፍርዱ ለእርስዎ እተወው አለሁ። የትግራይ ሕዝብ ተ.ሃ.ሕ.ትን አይደግፋትም ለሚለው ከርክር ፍፁም አሳማኝ ቃል አይደለም አዎ በመጠኑ አገር ወዳድ የሆኑ ይኖራሉ። በተለይ አብዛኛው በዳያስፖራ የሚኖረው የትግራይ ተወላጅ የተማረውም ሆነ ያልተማረው ሁሉ ተጋድሎ ሃርነት ትግራይ በቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የምትፈፅመው ግፍና በደል መኖሩ እያወቀ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት ዝምታ የመረጠበት ዋናው ምክንያት የትግራይ የበላይነት የምትለው ደካማና ኋላ ቀር መፈክር በማነገብ ነው። እንደ እኔው አመለካከት ከሆነ ይህ አይነቱ አስተሳሰብ ግዜው ያለፈበት የበሰበሰ አመለካከት ነው። ለሁላችን የሚበጅ መስሎ የሚታየኝ አንድ ብሩህ ነገር ቢኖር ሁላችንም በጋራ፤ በመተዛዘን፤በመከባበር፤በዕኩልነትና በሰላም መኖር የምንችለው ሁሉም ዜጋ የተሳተፈበትና የተግባባበት መተዳደርያ ደንብና ህግ በሰለጠነ መንገድ ቀርፀን ተግባር ላይ ስናውለው ብቻ ነው። የዛሬዎቹ የደደቢት የቀን ሽፍቶች ባወጡት ህገ ደንብ የማይመሩ አንዱን አካባቢ ወይም ግለሰብን ለመግደል፤ለመዝረፍና ለመወንጀል ሲፈልጉ በአንድ ምሽት የሚቀየር መተዳደርያ ደንብ ከሆነ አሁንም ያ ያልታደለው ሰርቶ አደር ገበሬውም ሆነ በላቡ አዳሪ የአምባ ገነን መሪዎች የጥይት ማብረጃ ከመሆን የሚያድነው አንድም ምክንያት አይኖርም። የአፍ ዴሞክራቶች በተግባር ግን ነብሰ ገዳዮች ተ.ሃ.ሕ.ት ተብየዎች ከጀርመኑ ናዚ ፋሽስትና ከደቡብ አፍሪካው ነጭ አፓርታይድ መንግስት በላቀ በህዝባችንና በአገራችን ላይ ይህ ቀረ ሊባልለት የማይችል ግፍ፤እልቂትና በደል አድርሰዋል። እንዲህ አይነት በደል ከሚያደርስ የሽፍቶች ጥርቅም " ወድ ላህምና (የቤታችን እንስሳ) እያልክ ከበሮ መደለቁ ከቀሪው ዘጠና አምስት ሚልዮን ሕዝብ ጋር አብሮ መኖር ይቻላል ውይ?

ወደ ተነሱበት የወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት አርዕስት ልመልስዎትና ይህ ህብረተሰብ ፈሪሃ እግዚአብሔ የተላበሰው፣ግብረ ገብነት፣ሰባአዊነት፣ትሁትና ታማኝ፣ርህሩህ፣ ጀግና አገር ወዳድና ለነፃነቱና ለዳር ደንበሩ ግንባሩ ለጥይት የሰጠና የሚሰጥ ለመሆኑ ማወቅ ከፈለጉ የእንጨት ሽበቶቹና ነብሰ ገዳዮች እነ ስብሀት ነጋን ሳይሆን እንደ የተከበሩ የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩት  ልዑል ራስ መንገሻ ስዩምና አገር ወዳዱ አቶ ገረመድህን አርአያን ቢጠይቁ የዚህ ሕዝብ ታሪክና ማንነት ማወቅ ይችሉ ይሆናል። ያለፉት መንግስታት ከአሁኖቹ ሽፍቶች በማወዳደር ለስልጣናቸው ጥቅም ሲሉ ያንዱን ድርሻ መሬት ለሌላው ያድሉ ነበር በማለት የተጋድሎ ሃርነት ትግራይን በደልና ግፍ ሊያቃልሉ በመጣርዎ እጅግ በጣም ያስተዛዝባል። የወልቃይት ጠገዴና የጠለምት ህዝብ በተጋድሎ ሃርነት ትግራይ ይህ ቀረ የማይባል የዘር ማጥፋት እልቂት ሲፈጸምበት አንዲት የማስተዛዘኛ ቃል እንኳ አልተነፈሱም ይህ የሆነበት ምክንያት የትግራይ ሕዝብ ተጠቃሚ በመሆኑ ነዋ። አይተ አብርሃ ደስታ የወልቃይትን ማንነት የሚያውቀውና የሚወሰነው ማንም ዘራፊና የመሬት ሌባ ሳይሆን በዝያች ወልቃይት የምትባለው መሬት ላይ እትብቱ የተቀበረው ውሳኔ እንጂ ተከዜ ተሻግሮ የመጣ የመቀሌ ተወላጅ በወሰነው መሆን እንደማይቻል ላበስሮት እወዳለሁ። ሃቁ በጠበንጃ ጋጋታ ሃይል የተዘረፈ ሁሉ ግዜውን ጠብቆ ይመለሳል በጀግንነትም ሆነ በትጥቅ ብዛት ወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምትንና አርማጭሆ ሕዝብ የሚወዳደር ማንም አልነበረም። የያዘነውን ይዘናል ሌላው (ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ) የሚለው ብሂል ለማንኛችንም አይጠቅምም ረጋ ብለን በማሰብ ለልጅ ልጆቻችን የማይሽር ቁስል ትተን ብናልፍ በታሪክ ለዘልዓለም ስንወቀስ እንዳንኖር ከተፈለገ መፍትሄው ከእጃችሁ ውስጥ ነው ያለው። '(በሎ ስበሮ ደርእሞ) የአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መፎከር ነው አሁን ያለነው የሰው ልጅ በእውቀት መጥቆ የሄደበት ሃያ አንደኛው ክፍለዘመን ነው ። ለሰላምና ለፍቅር ሁላችን አንድ አይነት መዝሙር እንዘምር።

ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ማንነቱ ማንም ሊለውጠው የማይችል ጎንደሬ አማራ ነው።

ሞት ለተ.ሃ.ህ.ት(ተጋድሎ ሃርነት ትግራይ)

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር።

08/26/2017፣